# ሕይወት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የወርቅ ኢዮቤልዩ ምክንያት በማድረግ፣

"**አ.አ.ዩ. በ50ኛው- ትናንት፥ ዛሬ እና ነገ**" በሚል
አጠቃላይ ርእስ ከተዘጋጁት ውይይቶች ለአንዱ፣

**“Reflections on Life at AAU”** ለሚለው፣

ተዘጋጅቶ፥ **ኅዳር** 18/1993፥ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋካልቲ አዳራሽ
የቀረበ።

**ፈቃደ አዘዘ**
**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል**

# ሕይወት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ፈቃደ አዘዘ

ርእሱ÷ "ዩኒቨርሲቲው ከተመሰረተ ጀምሮ እስከዛሬ ስላለው ሕይወት ተናገር" የሚል ይመስላል፡፡ እንዲህ ማለቱ ከሆነ÷ የሚጠበቅብኝን ለሟሟላት እንደማይቻለኝ ከወዲሁ መግለጽ እሻለሁ፡፡ ምክንያቴም በጣም ቀላልና ግልጽ ነው፡፡ እድሜያችን እኩል የሚባል ያህል ስለሆነ እኔ ስለርሱ እርሱም ስለኔ የማናውቀው ብዙ አለ፡፡ ደግሞም÷ ለማንኛውም ሰው ቢሆን÷ ባጭር ማሳሰቢያ በተሰጠ ዕድል÷ በ50 ዓመት ውስጥ የተኪያሄደውን "የመምህራንና የተማሪዎችን ምሁራዊና ባህላዊ ሕይወት÷ የመምህራንንና የተማሪዎችን ስነምግባር÷ የመምህራንንና የአስተዳደር ሠራተኞችን የስራ ቅልጥፍናና የሙያ ኤቲክስ÷ የጾታን ጉዳይ÷ በዩኒቨርስቲው እና በተማሪዎች÷ በሠራተኞችና በመምህራን መሀከል የነበረውን እና ያለውን ግንኙነት ወዘተ" [1] ውል ባለው መንገድ በቁዘማ መዳሰስ ያስችግራል፡፡ "ከ50 ዓመት በኋላ የሚመረምረን ይመጣል"ን ሳያስቡ የተጻፉትን ልዩ ልዩ ጽሁፎች አገላብጦ÷ ከየዘመኑ ተማሪዎች ÷ መምህራን እና የአስተዳደር ሠራተኞች ልዩ ልዩ አስተያየት ያላቸውን÷ በተለያየ የትምህርትና የሥራ ደረጃ ያገለገሉትን አነጋግሮ በምርምር ላይ የተደገፈ ነገር ልናገር እንዳይባል ደግሞ ጠቀም ያለ ጊዜ ሊያስፈልግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፈንታው ከመደበኛ የስራ ገበታ ጋር ጊዜን እና ሃሳብን÷ ካሁኑ ይበልጥ÷ ሊካፈል ሆነ፡፡ ይህ ሁሉ ቢደረግ እንኳ የሚገኘው ውጤት እንደራስ ትዝታ እያዋዛ ስሜትን እና አእምሮን እያነቃቃ የሚያዝናና እና የሚያስተምር አይመስልም፡፡ እርግጥ÷ የዛሬውንና የወደፊቱን የዩኒቨርስቲ ሕይወት ለማሻሻል የምሩን (seriously) የሚያስብ ድንገት ቢኖር÷ አንዳንድ መረጃ እየሰጠ ፍንጭ ሊያመላክት ይችል ይሆናል፡፡

---

[1] በነዚህ ርእሶች ላይ እንድቆዝም (reflect እንዳደርግ) እድል የሰጠኝ÷ ከአካዳሚክ ም/ፕሬዝዳንት ቢሮ የተላከ ደብዳቤ የደረሰኝ ጥቅምት 03/1993÷ በ9፡58 ሰዓት ነው (የተጻፈው ጥቅምት 01/1993 ነው፡፡) ለመዘጋጀት የነበረኝ ጊዜ ከኅዳር 03-13/1993 (በኋላ በራሱ ምክንያት እስከ 17 ሆኖልኝ ተገኝቷል) ብቻ መሆኑን እያወቅሁ የቻልኩትን ልሞክር በሚል ነው "እድሉ"ን የተቀበልሁት፡፡ (እስከ ኅዳር 02 ድረስ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ኢንተርናሽናል ኮንፍራንስ ላይ÷ ለፕሌነሪ ጉባዔ የማቀርበውን እንዲሁ ባጣዳፊ ማዘጋጀት ነበረብኝ፡፡)

በዚህች አጋጣሚ ሦስት ነገሮችን ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡ በመጀመሪያ ካንዳንድ ሰነዶች በሰበሰብኳቸው መረጃዎች መሠረት የዩኒቨርሲቲ ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር ለወጣቶቹ በጨረፍታ ለማሳወቅ፥ ጎልማሶቹን ደግሞ ለማስታወስ እሞክራለሁ፡፡ ቀጥዬ ደግሞ፥ እኔ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበርኩባቸው ዓመታት ሲኖር ከነበረው ሕይወት የማስታውሰውን፥ በቃሌ፥ በጥቂቱ አነሳለሁ፡፡ በመጨረሻ በኢትዮጵያ የዩኒቨርሲቲ ሕይወት ውስጥ ጥሩ መከሰት ተከስቶ ብልጭ ብሎ የጠፋውን፤ በወቅቱ በዚህ ክስተት ውስጥ ያለፉት እና ዝናውን ብቻ በመስማት የምናውቀው ግለሰቦች ሁሉ እስከዛሬ የምንገኘውን፤ ወይም ትዝታው ብልጭ ሲልብን በቁጭት የምንብሰለሰልለትን ቁምነገር በሩጫ አነሳለሁ፡፡ ይህ ቁምነገር የዱሮው "የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ቀን" የግጥም ባህል ነው፡፡

## 2. <u>የዩኒቨርሲቲ ሕይወት ባንዳንድ ሰነዶች መሠረት</u>

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከተቋቋመ ጀምሮ በግቢው ውስጥ የነበረውን ሕይወት ሰብስቦ፥ በውል አደራጅቶ፥ በዘርፍ በዘርፍ ከልስፎ፥ አጥንቶና ተንትኖ የተጻፈ መጽሐፍ ቢኖር ምንኛ ድንቅ ነበር፡፡ የወንዶችና የሴት ተማሪዎች ግንኙነት፤ የተማሪና የመምህር ግንኙነት፤ የስፖርት፥ የጋዜጣ፥ የሙዚቃ፥ የተውኔት፥ የክርክር፥ የስነጽሁፍ እና የዲስኩር እንቅስቃሴዎች፤ የተማሪውና የጥበቃ ሠራተኞች ድብብቆሽና ፍጥጫዎች፤ የምግብ ዓይነቶችና የተማሪና የምግብ ቤት ሠራተኞች ግንኙነቶች፥ የተማሪውና የቤተሰብ፥ የተማሪው እና የአካባቢው ነዋሪ፤ በጥቅሉም የተማሪው፥ የመምህሩ፥ የሠራተኛው እና የዩኒቨርሲቲው እና የማኅበረሰቡ በተለይ ደግሞ ተማሪውና መምህሩ ከመንግስታት ጋራ የነበራቸውና ያላቸው ግንኙነት፤ ከተለያዩ ትረካዎች ጋር እየተያያዘ፥ ከተፈጸሙ ድርጊቶች ጋር እየተመላከተ ተነግሮ፥ ተጽፎ እና በሌላም መንገድ ተቀርሶ ቢሆን እንዴት መልካም ነበር፡፡ እኛ ግን፥ ከጥንት ጀምሮ ሰዎች ስለኖሩት ሕይወት (ስለበሉት፥ ስለጠጡት፥ ስለለበሱት፥ ስላሰቡት፥ ስላለሙት፥ ስለዘፈኑት፥ ስላለቀሱት፥ ስለሞቱለት፥ ስለተገደሉበት ወዘተ.) ታሪክ ከመጻፍ ይልቅ፤ የቅዱሳንን እና የመሪዎችን ገድልና ተአምር በንቃት ወደመጻፉ ያጋደልን ስለሆንን እንደዚህ ዓይነቱን ጽሁፍ በቅርብ ጊዜ ማግኘት የሚቻለን አይመስለኝም፡፡ [2] ስለዚህ፥ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ቤተመጻሕፍት ለመገልገል

---

[2] እዚህ ጋ ቆም ብሎ የኖርዌይዋን ተወላጅ ራንዲ ሮኒንግ ባልስቪክን ከአክብሮት ጋር መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1985 በታተመው፥ Haile Sellassie's Students: The Intellectual and Social Background to Revolution, 1952-1977 በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሕይወት፥ ከፍ ብዬ ከጠቀስኳቸውና ከሌሎች ብዙ የተማሪ ጋዜጣዎችና መጋዚኖች ከተጻፉ ጽሁፎች መረጃ እየሰበሰቡ ብዙ ጠቃሚ ነገር ጽፈዋል፡፡ የተማሪውን አኗኗር በሚመለከት በብዙ ድካም አንድ የሚያወያይ ጽሁፍ የጻፉ እርሳቸው ብቻ ይመስሉኛል፡፡ ስለጋዜጦቹ የሚሰጧቸው ማጠቃለያዎች ብዙ ጊዜ የሚያከራክሩ ቢሆኑም የሠሩት ሥራ አልፌ ሰለሆነ ከልብ ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ሀገሪቱንና ባህሎቿን ከርሳቸው የበለጠ የሚያውቁና በትምህርት የበሰሉ ኢትዮጵያውያን በነዚህ ጋዜጦች፥ የዩኒቨርስቲ አስተዳደር ሪፖርቶች፥ እና በየዘመኑ ከኖሩ ሰዎች ጋር በሚደረግ የኢንተርቪው መረጃ ሌላ ሙከራ በቅርብ ጊዜ ቢያደርጉ ይህንን መሠረታዊ

በቻልኩባቸው ባለፉት 10 ቀናት የቃኘኋቸው ጋዜጦች፥ "ጆርናሎች"፥ "ኒውስሌተሮች" እና "መጋዚኖች"፤ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ፥ ስለዘመኑ የኑሮ ሁኔታ የተዉዋቸውን ዱካዎች ይዤ ስላልነበርኩበት ዘመን አንዳንድ ነጥቦች ላንሳና፥ ከዚያ ወዳየሁትና ወደኖርኩበት ዘመን እመለሳለሁ::

በ"የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም" ቤተመጻሕፍት ያገኘሁት የመጀመሪያው የተማሪ "ጋዜጣ" UC Calls የሚል ነው:: [3] የዚህ ጋዜጣ የመጀመሪያና ሁለተኛ "እትም" [4] ቀን የላቸውም:: ቁጥር 3 ላይ የተጻፈውን ቀንና ሳምንታዊነቱን የሚጠቅሰውን ቃል ይዘን እ.ኤ.አ. (Nov.1956 በኛ አቆጣጠር ጥቅምት 1949 የመጀመሪያ ሳምንት መውጣቱን መገመት እንችላለን:: የተማሪዎች የማስታወቂያ ፕሬዝዳንት (President of Publicity) አክሊሉ ለማ በመጀመሪያው ቁጥር ርእሰ አንቀጽ ላይ እንደገለጸው የጋዜጣው ዓላማ ልዩ ልዩ የተማሪ ክበቦች የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እና ተማሪው ማወቅ ይገባዋል የሚሏቸውን በከተማው ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን በየቅዳሜው፥ ጠዋት ማሳወቅ ነው:: በተጨማሪም ቀልዶችንና ዘመናዊ እንቆቅልሾችን (quizes) በማውጣት ተማሪውን እንደሚያዝናኑም ገልጿል:: ተማሪዎቹ፥ የእንቆቅልሾቹን መልሶች ማስታወቅ ያለባቸው ለስብሐት ገብረ እግዚአብሔር፥ ለተሻገር ውቤና ለአክሊሉ ለማ መሆኑን እና ብዙ ጥያቄዎችን ለመለሱ ሽልማት የሚሰጥ መሆኑን ርእሰ አንቀጹ ገልጿል::

ከቁጥር 4 በኋላ የተጠረዘ፥ ቀንና ቁጥሩ ግን ባልተገለጸ የጋዜጣው እትም ላይ፤ ጋዜጣው በየሳምንቱ ከመውጣት ይልቅ በየ15 ቀኑ እንደሚወጣ ተነግሮ የዚህም ምክንያት የጽሁፍ እጥረት መሆኑ ተገልጿል:: በተመለከትኳቸው አስራ አንድ ጋዜጦች ውስጥ በከተማ ሲኒማ ቤቶች የሚታዩ ፊልሞች፥ የቤት ውስጥ ጨዋታዎች፥ "የአርቲስቶች ማኅበር" አባል እንዲሆኑ ተማሪዎችን የሚቀሰቅሱ ጽሁፎች፥ የሀገር ፍቅር ማኅበር ተጫዋቾች ደጋግመው ተማሪውን ማዝናናታቸውን

---

የዩኒቨርሲቲ "ምሁራዊ፥ ባህላዊ እና ዘለቄታዊ አኗኗር" ላቅ ያለ ፍች ይሰጡታል ብዬ አስባለሁ:: በተለይ የሀገራችንን "የሃሳብ ታሪክ (History of Ideas)" የሚያጠኑ ጎበዛዝት አንድ ትልቅ ፈተና፥ የዚህን ግቢ ታሪክ፥ በሁለንተናዊ ገጹ፥ ጊዜ ፈጅቶ፥ ለመተንተንና እና፤ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ፥ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ሕይወት ላይ የነበረውንና ያለውን በጎና እኩይ አስተዋጽኦ እማሳየት ላይ ይመስለኛል:: በቡድን ተከፋፍሎ በእቅድ የሚሠሩት እንጂ በግለሰብ የሚቀመስ ሥራ አለመሆኑ መቸም እርግጥ ነው:: ዛሬ በፖለቲካል ሳይንስ ክፍለትምህርት የሚሰሩት ሰዎች የተለያየ የፖለቲካ ልምድ አንድ ጥሩ መነሻ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም::

[3] ከዚህ በፊት "Writer’s Club" ያወጣው ባለአንድ ገጽ "ጋዜጣ" እንደነበር University College Journal ላይ እተጻፈው ርእሰ አንቀጽ ውስጥ አንብቤያለሁ (እ.ኤ.አ. 1958፡ 4):: ጋዜጣውን ፈልጌ አላገኘሁትም:: ባልስቪክም ያየችው አይመስለኝም (Balsvik, 71 & 78)::  ጽሁፉ ባለ አንድ ገጽ እንደነበር፥ በየ15 ቀኑ የሚወጣና እ.ኤ.አ. ከ1952-1953 የቆየ እንደነበር ከፍ ብዬ በጠቀስኩት ርእሰ አንቀጽ ውስጥ ተገልጿል:: ርእሰ አንቀጹ፥ ስለተማሪ ጋዜጦች በስፋት የሚያጠና ሊመለከተው የሚገባ መሆኑንም መጥቀስ ተገቢ ይመስለኛል::

[4] አንባብያን በዚህ ቃል አገባብ እንዳይሳሳቱ በማሰብ ነው በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ያኖርሁት:: በስቴንስል ላይ ተተይቦ የተባዛ እንጂ በማተሚያ ቤት የታተመ አይደለም::  ጋዜጣ የሚለውንም ቃል በትእምርተ ጥቅስ ያኖርሁት አማራጭ ቃል በማጣት ነው::

የሚያመለክቱ ጽሁፎች÷ እና ስለ ፎተግራፍ ክበብ የመጀመሪያ ስበሰባ የተጻፈ ዜና ወጥተው ተመልክቻለሁ:: በመጀመሪያው እትም "Is Emancipation of women beneficial to society?" በሚል ርእስ ክርክር እንደተደረገ እና ርእሱን በመደገፍ እና በመቃወም የተከራከሩት ሰዎች ስምም ተገልጿል:: ገና በዚሁ እትም÷ ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ተማሪዎች ጽሁፍ እንዲያቀርቡ ጥሪ አቅርቧል:: ቁጥር 11 ላይ አስፋው ዳምጤ ሶስት ጽሁፎች በእንግሊዝኛ ሶስት በአማርኛ፤ በቁጥር 13 ላይ ደግሞ 4 በእንግሊዝኛ ሶስት በአማርኛ ጽፎ ስናገኝ የጋዜጣውን መቀጠል መጠርጠር እንጀምራለን:: ከቁ. 17 በኋላ የታተመ ጋዜጣ አላገኘሁም:: ስለዚህ ጋዜጣው ከNov.1956 - June 22/1957 ከፍ ብለን የጠቃቀስናቸውን ጽሁፎች አትሞ÷ አንባቢዎቹን ሳይሰናበት÷ ድንገት ተቋርጧል::

UC Calls÷ እቤተመጻህፍቱ ውስጥ ቅጂው የተገኘ የመጀመሪያው ጋዜጣ ስለሆነ ነው ዘርዘር አድርገን ሰላወጣቸው ጉዳዮች ለማስታወቅ የሞከርነው:: በየግቢው እና በየኮሌጁ ይወጡ የነበሩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ብዙ ስለነበሩ ሁሉንም በዚህ መልክ አቅርበን ወደ በሰለ ማጠቃለያ ለማምራት አንችልም:: የባልስቪክ ምርምር እስከሸፈነው እስከ 1970 ዓ.ም. የወጡት የተማሪ ጋዜጦች ቁጥር÷ በቫልስቪክ መዘርዝር መሠረት 29 ነበሩ:: ከነዚህ መሀል አዲስ አበባ የወጡት 25 ሲሆኑ በዓለማያ 01 እና በጎንደር 03 ነበሩ:: እውጭ አገር ይታተሙ የነበሩ ሌሎች 07 መጽሔቶችም ዘርዝራለች[5]:: እነዚህን ሁሉ መመልከት ሰለማይቻለኝ ሀገር ውስጥ ከወጡት በግል በየኮሌጁ ያልወጡትን÷ UC callsን ጨምሮ ስምንት [6] ያህሉን እና የቀኃሥ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል÷ ቤተመጻሕፍት ባገኘሁት ቅጂ መሠረት ከኅቸተ.23/1969 (ከጥቅምት 1961) ጀምሮ÷ ያወጣውን Recent Events and ActivitiesN (REA) በመቃኘት ያስተዋልኩትን በጣም ባጭሩ እገልጻለሁ:: በተለይ የማተኩረው ግን ብዙ ጽሁፍ በወጣባቸው በ REA እና በ News & Views (NV) ላይ ይሆናል:: ይህም ቢሆን ከሌሎቹ ለመለየት ሲባል÷ "ትኩረት" ይባል እንጂ ባብዛኛው ፈጣን ቅኝት ነው::

---

[5] ወጣቱና ጎልማሳው ተመራማሪ ፈልገው እንዲመለከቷቸው ዝርዝራቸውን ለማቅረብ ተገፋፉሁ፤፤ *The Lion Cub* (Great Britain); *On the Trial of Sheba* (India); *Jesame* (Middle East); *Challenge* (North America - New York); *Tewodros* (United Kingdom); ታጠቅ(Mimeographed in Stockholm, Sweden. ; and ትግላችን (Mimeographed in Stockholm, Sweden).

[6] *UCAA Newsletter, News & Views, University College Journal, Struggle, Something*, and እንዲህ ነው:: ባልስቪክ የመጨረሻዎቹን ሁለት የስነጽሁፍ መጽሔቶች "የተማሪ ሕትመቶች" በሚለው ክፍል አላሰፈረቻቸውም::

UCAA Newsletter[7] እግቢው ውስጥ የሚኪያሄዱ ተግባራትን በዜና መልክ ያቀርባል። ለምሳሌ ስለትያትር መታየት፥ ሰለወንዶች ተማሪዎች "ግሊ ክለብ"፥ ሰለሴቶች ተማሪዎች "ኮራል (choral) ክለብ"፥ ስለስፖርት፥ ስለ 'አሉምናይ' (የቀድሞ ተማሪዎች)፥ ስለ የሀገር ፍቅር ትያትር ቤት ጥበባዊ ዝግጅት በኮሌጁ፥ ስለ UC Journal ቁጥር 1 መውጣት ዜና ያቀርባል። ፒየር ኮምባ የተባለ ፈረንሳያዊ በሠራው መዘርዝር መሠረት 450 የአማርኛ መጻሕፍት መኖራቸው መነገሩም ለማኅበረሰቡ በዜና መልክ ተነግሯል። በኢትዮጵያ ምሳሌያዊ ንግግሮች ውስጥ ስላለው የበሰለ ሕዝባዊ እውቀት አንድ የውጭ ዜጋ፥[8] ስለ አጠቃላይ የህክምና ሳይንስ ዶ/ር (ዛሬ ፕሮፌሰር) አሥራት ወልደየስ[9]፥ ስለትምህርት ጉዳይ አቶ ሚሊዪን ነቅንቅ[10] ንግግር ማድረጋቸው ተጠቀሷል። ሶስት የንግግር/የዲስኩር ውድድሮች (Oratorical Contests) መካሄዳቸውን፥ ባንደኛው ላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ መካፈላቸውንና፥ የዊንጌቱ ገበየሁ ፈሪሳ አንደኛ፥ የቀኃሥ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ጌታቸው ጠብቄ ሁለተኛ መውጣቸው በዜና መልክ ቀርቧል።[11] በሶስተኛው ውድድር ላይ ንጉሠ ነገሥቱ መገኘታቸውም ተጠቅሷል።[12] የአማርኛ የግጥም ውድድር መኪያሄዱ፥ ስሙ ባልተጠቀሰ ዳኛ አስተያየት ደግሞ ግጥሞቹ፥ በቴክኒክና በጭብጥ (በተለይ በሁለተኛው) ከተለመደው የአማርኛ ባህላዊ አገጣጠም ያፈነገጡ መሆናቸው ተዘግቧል።[13] ክርክሮቹ (debates) መደረጋቸውና የአንደኛው የክርክር ርእስ "ለሀገሪቱ ይበልጥ የሚሠራ ገበሬ ነው፥ በትምህርት ቤት የሠለጠነው?" የሚል እንደነበርም ተገልጿል። አበበ አምባቸውና ሰሎሞን ዴሬሳ "በትምህርት ቤት የሠለጠነው ነው" የሚለውን ሃሳብ ደግፈው ሲናገሩ፣ ስዩም ገብረ ሥላሴ እና አወል አደም ደግሞ "ገበሬው ነው" የሚለውን ሃሳብ ደግፈው ተከራክረዋል።[14] ያንደኛው የዲስኩር ውድድር ርእስም "ያሁኑ ትውልድ የወደፊት ኃላፊነትና ተግባራቱ"[15] የሚል ነበር።

ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለጹትን ጉዳዮች በመረጃ ደግፌ ያቀረብኩት ባንድ በኩል ምንምን ተግባራት ይከናወኑ እንደነበር ለማሳወቅ ነው። ሌላው ምክንያት፥ ስላለፈ ዘመን የሚነገር ነገር፥ ብዙ ጊዜ የሚጋነን እና በተለያዩ አድማጮች ዘንድ በተለያየ የጥያቄና የጥርጣሬ ስሜት የሚታይ ስለሆነ በመረጃ የተደገፈ ነገር ግን ይህንን ስሜት በጣም ስለሚያቀዘቅዝ ነው።

---

[7] በኢ.ጥ.ም.ተ. ቤተመጻሕፍት ተጠርዘው የሚገኙት ቅጂዎች የሚጀምሩት "Thursday, Nov.28,57" የሚል ቀን በተጻፈበት በቁጥር 05 ነው። ከ1-4 ጥራዙ ውስጥ የሉም። ያየሁት የመጨረሻ ቅጅ ቁጥር 30፥ July 3, 1958 ነው። ቀኑ ተደልዟል። 03 ይሁን 04 ለመለየት ያስቸግራል።

[8] UCAA Newsletter, No.7 Dec.12, 1957.

[9] UCAA Newsletter, No,19 March 21, 1958.

[10] Ibid.

[11] UCAA Newslwtter,No.21 May 2,1958.

[12] UCAA Newsletter, No.28. June 19,1958.

[13] UCAA Newsletter,No.22. May 9,1958.

[14] UCAA Newsletter, No.17. March 7,1958.

[15] UCAA Newsletter, No.15. February 21, 1958.

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ መጨረሻና በ1960ዎቹ ይኪያሄዱ የነበሩ ምሁራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች በጣም እየጨመሩ መሄዳቸውን News & Views[16] ን፥ Recent Events & Activities[17] ን፥ Struggle[18] ን Something[19] ን እና "እንዲህ ነው"[20]ን ፥ በመመልከት መገንዘብ ይቻላል። ከፍ ብለን የዘረዘርናቸውን፥ በየኮሌጁ የሚታተሙትንም መጽሔቶች ማስታወስ አለብን። በነዚህ ጋዜጦችና መጽሔቶች ውስጥ ዝርዝራቸው የሚያታክት፣ ጊዜ ወስዶ በሚሠራ ምርምር ካልሆነ በቀር እንዲህ በሩጫ በመልክ በመልኩ ማደራጀት የማይቻለኝ ተግባራት እንደሚከናወኑ ተመልክቻለሁ። ብዙ ግጥሞች በእንግሊዝኛ ታትመው ይገኛሉ፤ የዲስኩር ውድድሮችና ክርክሮች ባማርኛና በእንግሊዝኛ በብዛት ይኪያሄዱ፥ ሙያዊ ንግግሮች (lectures) በየግቢው ይደረጉ ነበር። የተማሩ የመንግስት ሹሞች፥ አምባሳደሮች፥ የውጭ ሀገር እንግዶችም በተለያዩ ርእሶች ላይ ይናገሩ ዩኒቨርሲቲውንም ይጎበኙ ነበር። የተማሪ ክበባት በየመስኩ ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። በተማሪዎች የሚመሩ የሙዚቃ፥ የተውኔት፥ የስፖርት ፕሮግራሞች ብዙ ነበሩ ማለት ይቻላል።

ከNovember 1959 ጀምሮ እስከ December 1960 መፈንቅለ መንግሥት ድረስ ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ቁጥጥር ነጻ ስለመውጣት፥ ስለ ፕሬስ ነጻነት እና ሰለ ዲሞክራሲ መጻፉ ጥቂት ጎላ ብሎ የሚታይ ነበር። የተማሪዎች ዲን ሚስተር ግሪንፊልድ እና ምክትላቸው አቶ ግርማ አማረ ከተማሪዎች ለቀረቡላቸው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ነክ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡበት ስብሰባ ተኪያሂዶ የጥያቄና መልሱ ፕሮግራም እንደተኪያሄደ በNews & Views ተገልጾ ነበር[21]። ብሔራዊ የተማሪዎች ማኅበር ለማቋቋም የተዘጋጀ ሕገ ማኅበር (constitution) በስብሰባ ላይ ውይይት ይደረግበት ነበር[22]። ታኅሣሥ 1953 መፈንቅለ መንግሥት ሲኪያሄድ አልጋ ወራሹ በሬድዮ ያደረጉት ንግግር በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ ታትሟል[23] ። ከዚህ በኋላ የዲሞክራሲንና የነጻነትን

---

[16] Published by the students, University College of Addis Ababa. በኢ.ጥ.ም.ተ. ቤተመጻህፍት ተጠርዘው የሚገኙት ቅጅዎች የሚጀምሩት October 9, 1959 በወጣ ጋዜጣ ነው። የመጨረሻው ደግሞ March (?), 1965 የወጣው ነው።

[17] Published by Office of Public Relations News Bureau. በዚሁ ቤተመጻሕፍት ተጠርዘው የሚገኙት ቅጂዎች የሚጀምሩት በቅጽ 1 ቁጥር 1፥ October 23/1969 ነው።

[18] Published by The University Students' Union of Addis Ababa. Vol 1, No.1. March 23, 1967.

[19] ይህ የስነጽሁፍ መጽሄት በእንግሊዝኛ መውጣት የጀመረው እ.ኤ.አ. በ1962 መሆኑ እና እሰከ 1968 መታተም መቀጠሉ ይታወቃል (Fekade, 1985፡ 35)።

[20] እሽፋኑ ላይ፥ "እንዲህ ነው፥ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የሥነ ጽሁፍ መጽሔት፥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፥ አዲስ አበባ ጥር 1952 ዓመተ ምህረት። 1ኛ ዓመት ቁጥር 1፥ በብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።" የሚል የተሟላ መረጃ የያዘ ነው። ሁለተኛውና እኔ እስከዛሬ ያየሁት የመጨረሻው የመጽሔቱ 2ኛ ዓመት ቁጥር 1፥ በ1958 የወጣው ነው። እስሙ ላይ ሁለት መሠረታዊ ለውጦች ይታያሉ። አንደኛው "የአርትስ ፋክዩልቲ የሥነ ጽሑፍ መጽሔት" ማለቱ ሲሆን ሁለተኛው በአዘጋጅነት፥ በማደያ ክፍል ሹምነትና በስነ ጽሑፍ ቦርድ አባልነት ስማቸው እውስጥ የተዘረዘረው በሙሉ መምህራን መሆናቸው ነው። የመጀመሪያው ቁጥር አዘጋጅ ተማሪ ብረሀነ መስቀል ረዳ ነበር። ረዳት አዘጋጅ መምህር በእምነት ገብረ አምላክ ነበሩ። ስድስቱ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ተማሪዎች ሲሆኑ ከስምንቱ የሥነ ጽሑፍ ቦርድ አባላት ሶስቱ መምህራን ሲሆኑ ሌሎቹ ተማሪዎች ይመስሉኛል (??)።

[21] News & Views, October 20, 1960.

[22] News & Views, November 27, 1959.

[23] News & Views, December 16, 1960.

ጉዳይ የሚያነሱ ጽሁፎች መውጣት ጋብ ይላል፡፡ የክርክር ክበብና የሌሎች ክበባት እንቅስቃሴዎችም በጣም እየቀዘቀዙ በመሄዳቸው በርእሰ አንቀጹ ላይ ሁኔታውን በመተቸት ተጽፏል[24] ፡፡ ያንኑ ተከትሎ እንቅስቃሴው እንደቀድሞው እንዲቀጥል ጥሪ የሚያደርግ ጽሁፍ ቀርቧል[25] ፡፡ የክርክርና[26] የዲስኩር [27] ፕሮግራሞች እንደገና መጀመራቸውን በኋላ ከወጡ የጋዜጣው እትሞች ማወቅ ይቻላል፡፡ ከዚያ በሰፊው ተዘግቦ የምናገኘው የኮሌጅ ቀን አከባበር ነው[28] ፡፡

ይኸው ጋዜጣ (News and Views) ለማኅበረሰቡ ልዩ ልዩ ዜናዎችን እና ጠቃሚ መረጃዎችን ያቀርብ እንደነበር መጥቀስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በሞት የሚለዩ ሰዎችን፣ ቤተመጻሕፍት ውስጥ የሚጨመሩ አዳዲስ አገልግሎቶችን፣ የመምህራንን መቀጠር፥ ለትምህርትና ለኮንፍራንስ ወደውጭ መሄድና መመለስ በየዓመቱ ወደዲዩኒቨርሲቲው የሚገቡትን ተማሪዎች ጠቅላላ ቁጥርና በየክፍለትምህርቱ የተመደቡትን፣ አፍሪካ ነክ ጉዳዮችን፥ ተማሪዎች ለመስክ ምርምር የሚያደርጉትን ጉዞ፣ ለፋካልቲ ካውንስል አባልነት የሚመረጡ መምህራንን ስም እና የካውንስሉን አንዳንድ የውይይት ርእሶች፣ ለተማሪ ማኅበር መሪነት የሚደረጉ የምረጡኝ ዘመቻዎችን እና የመሳሰሉትን በዜና መልክ ያቀርብ ነበር፡፡ ከሚያቀርባቸው አኃዛዊ ጠቃሚ መረጃዎች የሚከተለውን ጠቀሼ በቀጥታ ወደሌላ ነጥብ አመራለሁ፡፡

> There were at 16-11-59 students in the College from fifteen different countries including Ethiopia. The names of these countries and the number of students representing them are as follows: Armenia 1, Ethiopia 376, Ghana 3, Greece 7,India 4, Kenya 9, Liberia 1, Nigeria 3, Sudan 2, Tanganyika 10, Uganda 2, U.K. 1, U.S.A.4, Yugoslavia 2, and Zanzibar 1, giving a total of 426 students in all.[29]

በተከታታይ ይወጡ ከነበሩት ሁለት አምዶች አንዱ "That will be the day when…" በሚል የሚቀርበው ነበር፡፡ በዚህ ርእስ ስር የሚጻፉት አስተያየቶች ብዙ ጊዜ በአንድ አጭር ዐረፍተነገር የተካተቱ ናቸው፡፡ ዓላማቸውም እያሳቁ መተቸት፥ ማሳወቅ፥ ማበረታታት፥ ማነቃቃት ወዘተ. ነው፡፡ ይህንን ጽሁፍ እንደማዘጋጅ የሚያውቅ አንድ መምህሬ፥ ብዙ ጊዜ ወደየግቢው እየተኬደ

---

[24] News & Views, January 26, 1961.
[25] News & Views, February 16, 1961.
[26] News & Views, March 9, 1961.
[27] News & Views, May 25, 1961.
[28] Ibid.
[29] News & Views, November 20, 1959.

ሰዎችን እና አካባቢዎችን በማጥናት የሚጻፍ መሆኑን ነግሮኛል[30]፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተለውን ልጥቀስ፡፡

**That will be the day when:**

- Baalu Girma wakes up in time for breakfast.[31]
- The students have nothing to say about the food.[32]
- Scholarship students can stay away from politics.[33]

ሌላው አምድ "Who is who in the UCAA Family" በሚል ርእስ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚሠሩትን የውጭ ሀገር እና የሀገር ውስጥ ዜጋዎች አጭር የሕይወት፥ የትምህርት፥ የምርምርና የሥራ ታሪክ የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የአቶ (ዛሬ ፕሮፌሰር) መስፍን ወልደማርያም የወጣበትን በመጥቀስ ስለዚህ ጋዜጣ የማቀርበውን እደመድማለሁ[34]፡፡

Recent Events & Activities (REA)፥ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው በቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል የዜና ቢሮ ከኝቸተኘበዠረ 23/1969 ጀምሮ ይወጣ የነበረ ነው፡፡ እስከ ዛሬ፥ አልፎ አልፎ የሚወጣ ስለሆነ የማተኩረው እስከ 1973 (እ.ኤ.አ.) እወጡትና ተጠርዘው ቤተመጻህፍት ያገኘኋቸው ላይ ነው፡፡ እውስጡ ይታተሙ የነበሩት ዜናዎች ምን ምን ዓይነት እንደነበሩ ዘርዘር አድርጌ ለመመልከት እሻለሁ፡፡ ይህንን የማደርገው በዚያን ጊዜ፥ ተማሪው፥ መምህሩ እና ሌላው የዩኒቨርሲቲ ማኀበረሰብ ስለዩኒቨርሲቲው ምን ያህል እያወቁ ይኖሩ እንደነበር ለዛሬዎቹ ለማሳየት ነው፡፡

REA በሞት ስለተለዩ አባላት አጭር ታሪካቸውንና ሥራችውን ጨምሮ ይጽፋል፡፡[35] ትምህርታቸውን ጨርሰው ስለሚመለሱ እና ከኮንፍራንስ ስለሚመለሱ [36] ኢትዮጵያውያን ዘርዘር አድርጎ ያቀርባል፡፡ የውጭ ፈታኝ (external examiner) ሆነው ሌላ ሀገር ሄደው ስለተመለሱ ሰዎች ልምድና፤[37] ሬጅስትራሩና ኮምትሮለሩ ለሥራ ሄደው ሲመለሱ የሄዱበትን ምክንያትና

[30] ዮናስ አድማሱ፥ ኀዳር 13/1993፥ በ11፡00 ሰዓት፡፡
[31] News & Views, February 23, 1961:4.
[32] News & Views, March 3, 1961: 3.
[33] News & Views, June 8, 1961: 6.
[34] News & Views, June 8, 1961.
[35] ለምሳሌ የMay 7/1970 ን፥ April 9/1971 ን ይመልከቱ፡፡
[36] November 6/1.969.
[37] May 25/1971.

ያከናወኑትንም ጠቅሶ ይጽፋል።[38] ስለአዲስ መምህራን መቀጠርም ዜና ይዘግባል።[39] ስኮላርሺፕ ለዩኒቨርሲቲው አባላት ሲመጣ፥ ለየትኛው ክፍል እንደመጣ፥ ስንት እንደመጣ፥ ተመርጠው ለትምህርት ለሚሄዱት ሰዎች ለትራንስፖርት፥ ለልብስና ለመኖሪያ የሚሰጣቸው ገንዘብ ልክና የሚያገኟቸው ሌሎች ጥቅሞችም በግልጽ ተዘግበው ይገኛሉ።[40] ይህ ተነግሮ አስራ አምስት ቀን ሳይሞላ ደግሞ 52 ኢትዮጵያውያን ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ እንደሚሄዱና 40 ያህል ደግሞ ትምህርታቸውን ጨርሰው እንደሚመለሱ ተገልጿል።[41]

ስለዩኒቨርሲቲው የውስጥ አስተዳደርም የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ እንዲያውቅ የሚደረጉ ጥረቶችም ይዘገባሉ። ለምሳሌ ከተለመደው የጉዞና የሥራ ሪፖርት በተጨማሪ በስልክና በደብዳቤ ብቻ የሚተዋወቁ 30 የአስተዳደር ሠራተኞች ይበልጥ ለመተዋወቅና የተሻለ የሥራ ግንኙነት ለማዳበር በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ወደ ላንጋኖ መሄዳቸው ተጽፏል።[42] የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎችን፥ ከዚያ ደግሞ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ተማሪዎችን፥ በተለያዩ ቀናት በአራት ኪሎ ምግብ ቤት እንደሚያነጋግሩ "Meet the President Programme" በሚል ርእስ ስር ተነግሯል።[43] ከዚያም 37 ገጽ ያለው የፕሬዝደንቱ ዓመታዊ ሪፖርት እንደወጣና በየፋካልቲውና በየኮሌጁ የሚኪያሄዱትን ፕሮግራሞች የሚገልጽ 340 ገጽ ሪፖርት በፖስታ ቤት ለየሚመለከታቸው ክፍሎች እየተላከ መሆኑ ተዘግቧል። [44]

በየኮሌጁ ስለሚከናወኑ ዐቢይ ጉዳዮችም ዜና ይነገራል። ስለቴክኖሎጂ ፋካልቲ መስፋፋት፥[45] ስለጤና ኮሌጅ መገምገም[46] እና ስለ ዓለማያ እርሻ ኮሌጅ የምርምር ሥራዎች[47] በተለያዩ እትሞች ላይ ተጽፎ ይገኛል። ስለምርምር ሥራዎች ለምሳሌ ስለ "ባቡን ባህርይ" ጥናት፥ ሪፖርት ተዘግቧል።[48] እውጭ ሀገር መጋዚን ላይ ሊታተም ስለተላከ ስለ "ኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ አገልግሎት" (Ethiopian University Service) ስለተጻፈ መጣጥፍ ርእሱንና የሚታተምበትን መጋዚን ጨምሮ ዜና ቀርቦ ይገኛል።[49]

---

[38] May 25/1971.
[39] April 9/1970.
[40] March 30/1972.
[41] April 13/1972.
[42] March 9/1971.
[43] October 16/1970.
[44] May 4/1972.
[45] April 9/1970.
[46] March 25/1971.
[47] November 30/1972.
[48] March 9/1971.
[49] May 4/1972. የመጣጥፉ ርእስ 'The Ethiopian University Service: a pioneer venture involvement of youth in national development" የሚል ሲሆን ጸሐፊው ዲን (ዛሬ ፕሮፌሰር) ስዩም ገብረ ሥላሴ ነበሩ። ሊታተም የተላከው Synergist ለሚባል ዋሽንግተን የሚታተም መጋዚን ነው።

የህግ ፋካልቲ ተማሪዎች በዓለም አቀፍ የ" Moot Court " ("የፌዝ ፍርድ ቤት" እንበለው) ሁለተኛ ወጥተው መመለስ፥ ከተደረገላቸው የሞቀ አቀባበል ጋር ተነግሯል፡፡ በዚህ፥ በተወሰነ ርእስ ላይ፤ የፍርድ ቤትን ስርዓት ተከትሎ በሚደረግ ክርክር ላይ የተሳተፉት ካፕቴን ጎሹ ወልዴ፥ አቶ አብዱ ዋሴ ዩሱፍ እና አቶ አሰፋ ጫቦ ነበሩ፡፡ ለፍጻሜ ውድድር ለመድረስ የቻሉት ከዛምቢያ ዩኒቨርሲቲ፥ ከኤግዚተር ዩኒቨርሲቲ (እንግሊዝ)፥ ከአርጀንቲና ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት እና ከላይቤሪያ የመጡትን ረትተው ነው፡፡ በመጨረሻም፥ በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች መሀል በተደረገ ተመሳሳይ ውድድር አሸናፊ ከነበረው ከሚያሚ ዩኒቨርሲቲ ወኪሎች ጋር ነበር የገጠሙት፡፡ በዚሁ ዜና መሠረት፥ የኢትዮጵያው ቡድን ሁለተኛ ይውጣ እንጂ ከተወዳዳሪዎቹ ሁሉ ምርጥ ተናጋሪ (Best Oralist) ሆኖ ተመርጦ ዋንጫ የተሸለመው ጎሹ ወልዴ ነበር፡፡[50] የፋካልቲው የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች የሆኑት ብርሃኔ ጊላ እና አሰፋ ጫቦ ለሌላ ተመሳሳይ ውድድር መመረጣቸው እና የሶስተኛ ዓመቱ ኤልያስ ኑር በተጠባባቂነት መመረጡ ተጠቅሷል፡፡[51]

ስለመጻህፍትና ስለልዩ ልዩ ባህላዊ እንቅስቃሴዎች በልዩ ትኩረት የተዘገበባቸው ሁኔታዎችም ነበሩ፡፡ የአቶ ሰይፉ መታፈሪያ <u>ዐፈር ያነሣ ሥጋ</u> ሲወጣ የሚከተለው ተጽፎ ነበር፥

> **ዐፈር ያነሣ ሥጋ፡** A 154 - page poetry book in Amharic, authored by Ato Seifu Metaferia (Amharic Department lecturer) is on sale. The book, which has 64 pieces, is written in 'chronological flashback', so to speak, going back from 1972-1943. A lecturer in the Amharic Department had this to say of the book: "It is worth reading." According to the author, there are 2000 copies on sale in the book-shops here in the capital and other places in the country.[52]

የዶክተር (ዛሬ ፕሮፌሰር) ታደሰ ታምራት **Church and State in Ethiopia 1270-1527**፥ የዶ/ር ሥርግው ሀብለሥላሴ **Ancient and Medieval Ethiopian History up to 1270**, እና የአቶ (ዛሬ ፕሮፌሰር) መስፍን ወልደማርያም **An Introductory Geography of Ethiopia**ም በዚሁ ጋዜጣ ላይ ከአንባብያን ጋር ተዋውቀዋል፡፡ "This week's book list" በሚል ርእስ ስር ቤተመጻሕፍት የገቡ የአዳዲስ መጻሕፍት ዝርዝርም ይቀርብ ነበር፡፡[53]

---

[50] May 17/19 92.
[51] April 5/1973.
[52] November 9/1972.
[53] January 11/1973.

የትምህርት ፋካልቲ የተማሪዎች ግንኙነት ኮሚቴ (Student Relation Committee) ዓርብ-ዓርብ ማታ አእምሮን ከማበልጸግ ጀምሮ እስከ ማዝናናት የሚሄዱ ብዙ ፕሮግራሞች ያዘጋጅ እንደነበር ተጠቅሶ ስለወደፊት እቅዳቸውም የሚከተለው ተጽፎ ይገኛል::

> ...Currently our students are planning activities such as: panel discussions, debates, film shows, field trips, talent show etc. to be given throughout the academic year.[54]

ከዚህ በኋላ በወጣ ሌላ ጽሁፍ ኮሚቴው በ"Creative Arts Centre" (ያሁኑ "የባህል ማዕከል") አዳራሽ ውስጥ ባለፉት ሁለት ዓመታት፣ በየሳምንቱ ዓርብ የውይይት ፕሮግራሞችና የፊልም ትርኢቶች ሲያቀርብ እንደቆየ ተነግሯል::[55] ከዚሁ ጋር ተያይዞም የኬኒዲ ቤተመጻሕፍት በዚያው ሰሞን አዘጋጅቶ ስለነበረው ስለ አራተኛው የግጥም ንባብ ተጽፎ ቤተመጻሕፍቱ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከኤዱኬሽን ፋካልቲ የተማሪዎች ግንኙነት ኮሚቴ ስራ ጋር ሊነጻጸር እንደሚችል ተጠቁሞ÷ ለሙከራው ምስጋና ቀርቦለታል::[56] ሌላው ዘለግ ያለ ጽሁፍ የቀረበበት ባህል ነክ እንቅስቃሴ "Orechestra Ethiopia Cultural Week" በሚል ርእስ ከኦርኬስትራው 10ኛ ዓመት በዓል ጋር ተያይዞ ለስድስት ቀናት የተዘጋጀው ፕሮግራም ነው:: የቡድኑ መሪ አቶ ተስፋዬ ስለዝግጅቱ ሲገልጹ "...six day cultural week will be highlighted by four lectures, an exhibition of traditional musical instruments from various parts of Ethiopia and a new repertoire of songs and dances."[57] ብለዋል:: ንግግር የተደረገባቸው አበይት ርእሶች "የኢትዮጵያ ሙዚቃ"÷ "የወታደር ሙዚቃ"÷ "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዳንሶች"÷ "የሬድዮ ሙዚቃ በኢትዮጵያ" ነበሩ:: ንግግሮቹ የተደረጉት በCreative Arts Centre (በዛሬው "የባህል ማእከል") አዳራሽ ነበር::[58]

ሌላው ከዚህ ጋዜጣ የምንረዳው የዩኒቨርሲቲ ሕይወት ከሴቶች ጋር የተያያዘ ነው:: ይህ ዛሬ ባንዳንዶች ከልብና ከምር የሚታከተለት፣ ቁጥራቸው በዛ ለሚል ደግሞ የ"ፈንድ" (የንግድ ወይም "የሽቀላ ገንዘብ" ማለቱ ይሻላል) ምንጭ እና የሥራ መስክ የሆነው የሴቶች ጉዳይ ዜና ተደጋግሞ

---

[54] ይህ የተገለጸው Mr. R. Capozzi÷ የኮሚቴው ረዳት ሊቀመንበር÷ ለአዘጋጁ በጻፉት ደብዳቤ ውስጥ ነው (የNovember 2, 1972ቅጅ ይመልከቱ):: በጊዜው የፋካልቲው ዲን የነበሩት ለፕሮግራሞቹ መቃናት ግምባር ቀደም አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ተገልጿል:: ስማቸው ግን አልተጠቀሰም::

[55] March 22/1973.

[56] March 22/1973.

[57] November 16/1972: 4.

[58] Ibid.

ይነሳ ነበር። ከAugust 9/1970 ጀምሮ ስለ "የዩኒቨርሲቲ የሴቶች ክለብ" በሚል የወጡት ጽሁፎች ጥቂት ስላልሆኑ ቢመረመሩ ሰለዘመኑ የሚናገሩት ጥቂት የሚባል አይሆንም። በተለይ የዛሬዎቹ የCERTWID ተመራማሪዎች እና የዩኒቨርሲቲው የምርኛ (serious) የጾታ አጥኚዎች እንዲቃኙት እጠቁማለሁ።

አንዳንድ ፕሮብሌሞችና የማኅበራዊ ኑሮ እቅዶችም በጋዜጣው ላይ ይወጡ ነበር። ለምሳሌ፥ የተማሪዎች ሻይ ቤትን መዘጋት፥[59] የመጻህፍትን ከቤተመጻህፍት መጥፋት ("መሰረቅ" ማለታቸው ይመስለኛል!)[60] ፥ የማየት የተሳናቸው ተማሪዎችን አንባቢ ማጣት (በጊዜው በፈቃደኛነት የሚመጡት ፈረንጆች ብቻ መሆናቸውን ጠቅሶ ኢትዮጵያውያኑ እንዲመጡ የሚያሳስብ)[61]፥ በዩኒቨርሲቲው የቴሌፎን ማውጫ ውስጥ የነበሩትን የትየባና የመረጃ ስህተቶች[62]፥ በአማርኛ የሚጻፍ መጣጥፍ መጥፋት[63]፥ የፈተናን ሁኔታ[64]፥ የሴቶች ተማሪዎችን[65]፥ በሚመለከት መጣጥፎች ይጻፉ ነበር። በመጨረሻ በተጠቀሰው ርእስ፥ የትምህርት ፋካልቲ የአራተኛ ዓመት ተማሪ የነበረው ኃይሉ ኢሳይያስ የጻፈው መጣጥፍ፥ በስላቅ የዘመኑን ሴት ተማሪዎች የሚተች ነበር። ሴቶች በልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደማይሳተፉ፤ ስለሴቶች ሚና በኢትዮጵያና በሌላው ዓለም ክርክርና ውይይት እንደማያዘጋጁ፤ ወደ ሶደሬና ወደ ሌሎች መታየት ወዳለባቸው መዝናኛ ቦታዎች ሽርሽር እንደማያዘጋጁ፤ "የዩኒቨርሲቲ የልጃገረዶች (የሴቶች) ቀን" ማዘጋጀት እንደማያስቡ፤ ለተማሪዎች ማኅበር ምክርቤት አባልነት ተወዳድረው እንደማያውቁ በአሽሙር ስልት በተጻፈ ጽሁፉ ይገልጻል።[66]

በዚህ ክፍል የማቀርበውን ከማብቃቴ በፊት፥ በጋዜጣው ውስጥ፥ በአኃዛዊ መረጃ ተደግፈው የሚቀርቡት አንዳንድ ጽሁፎች፥ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ከ1966 ወዲህ ከነበረው ሁኔታው ጋር ሲነጻጸር የፊተኛው ምን ያህል ግልጽ (transparent) እንደነበረ የሚጠቁሙ ማስረጃዎችን ልጠቃቅስ። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ይህንን ነጥብ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንሳቴ እንዳልሆነ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ከዚህ በታች ያሉትን መጥቀስ ነጥቤን ያጠነክራል። ለወደፊቱም ትምህርት ይሆን ይሆናል (ተስፋ አለመቁረጥ አይደል እዚህ ያደረሰን?) የሚል ግምት ሰላለኝም ነው ጉዳዩን እንደገና ማንሳቴ። የምጠቀሳቸው መረጃዎች በሙሉ ከ Recent Events & Activities ቅጽ 1፥ቁ.1፥ የOctober 23/1969 እትም ብቻ ይሆናሉ። ሌላውን መገመት ያንባብያን ፈንታ ይሆናል።

---

[59] March 25/1971.
[60] April 2/1971.
[61] April 2/1971.
[62] March 30/1972.
[63] May 11/1972.
[64] march 15/1973.
[65] April 5'1973.
[66] Ibid.

ወደዩኒቨርሲቲው አዲስ ስለገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከሬጅስትራር ቢሮ በመስከረም ወር የወጣውን እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡

“Total number 1531 (1st year only); Advanced Standing 189; Arts Stream 566;
Life Science Stream 317; Physical Science Stream 365; Public Health College 042;
TTE 104; Library Science Diploma 031; Directors & Supervisors 106; Freshman Girls
136.

Of the total

| | |
|---|---|
| 1454 | for degree |
| 239 | for diplomas |
| 27 | yet unclassified” |

“The figures show an increase of 17 over that of last year.”

ይህንን ትክ ብሎ ማጣጣሙን እንደገና ለአንባብያን እተዋለሁ፡፡

የኬኒዲ መታሰቢያ ቤተመጻሕፍት ሥራ ሶስት ዓመት መፍጀቱን ከተናገረ በኋላ ቤተመጻሕፍቱን ለተገልጋዮች ለማዘጋጀት የሚውሉ፥ ከውጭ የመጡ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ይዘረዝራል፡፡ የመጡት ወንበሮች፥ ሼልፎች፥ ጠረጴዛዎች እና ሌሎች ዕቃዎች በ116 ክሬት (crates) እንደተጫኑና እነርሱን ማደራጀት 60 ቀን ገደማ እንደሚፈጅ፤ የቤተመጻሕፍቱ የመቀመጫ ልክ 700፤ ሊይዝ የሚችለው መጽሐፍ ልክ 200,000፥ ለሕንጻው ሥራና ለልዩ ልዩ እቃዎች የወጣው 2.3 ሚልዮን ብር እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የቤተመጻሕፍቱን ልዩ ልዩ ክፍሎች፥ የሚሰጡትን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ገልጾ ከተባበሩት መንግሥታትና ከመንግሥት የተገኙ ኦፊሴላዊ እትሞች ያካተተና 30,000 ዶኩመንቶች ያሉት ክፍል እንዳለም ያስረዳል፡፡ ይሄንንም ትክ ብሎ ማጣጣምና፥ ከዛሬው ሁኔታ ጋርም በሩቅም በቅርብም ያለን ለማነፃፀር መሞከር ይገባን ይመስለኛል፡፡

በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ስለተዘረጋው አዲስ ስልክ ሲዘግብ የፈጀው 40,000 ብር መሆኑን፥ ስዊች ቦርዱ 75 የውስጥ እና 10 የውጭ መስመሮች ሊያስተናግድ መቻሉን ይናገራል፡፡ አሮጌው ከስድስት ኪሎ ወደ አራት ኪሎ፥ የአራት ኪሎው ወደአምስት ኪሎ እንደሚሄዱ፥ ይህም ሆኖ የስልክ አገልግሎት ገና በቂ እንዳልሆነ፥ የሕንጻና ጥገና ኃላፊው ያስታውቃል፡፡

የዩኒቨርሲቲ መምህራንን በሚመለከትም tenure ("ይርጋ" እንበለው?) ያገኙትንና እድገት የተሰጣቸውን ያቀርባል፡፡ ይርጋ ያገኙት 7 ፕሮፌሰሮች እና 7 ተባባሪ ፕሮፌሰሮች መሆናቸውን ከነስሞቻቸው ጠቅሶ÷ ከዚያም ይህ እድገት የተከናወነበትን የፋካልቲ ካውንስል የ1968 (እ.ኤ.አ.) ደንብ በይፋ ይዘረዝራል፡፡ አንድ የዩኒቨርሲቲ ሹምን በስም ጠቅሶ የትውልድ ዘመንና ቦታውን÷ የተማረባቸውን ዩኒቨርሲቲዎች፣ የሥራ ልምዱን (በዳይረክተርነትና በአማካሪነት በኢንተርናሽናል ደረጃ የነበረውን ልምድ ጨምሮ)፣ ስለ ከፍተኛ ትምህርትና ስላስተዳደሩ ስለጻፋቸውና ስላሳተማቸው ሶስት መጻሕፍት እና እድሜው 62 እና የሶስት ልጆች አባት ስለመሆኑ በዝርዝር ዘግቧል፡፡ ለተሾመበት ቦታ ያለውን ብቃት በኢርቱዕ ሰለሚጠቁም የማኅበረሰቡ አባላት ከዚህ ተነስተው ብዙ ነገር እንደሚያመዛዝኑ ግልጽ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት መረጃዎች የሕብረተሰቡ አባላት ስለዩኒቨርሲቲው ብዙ ነገር እንዲያውቁ ከማድረግ አልፈው ሰለ ሀላፊነትና ስለግልጽነት (transparency) በተዘዋዋሪ የሚያስተምሩት ብዙ ነው፡፡

በመጨረሻ÷ ጋዜጣው “Arts & Arts” ÷ “How About This!”÷ “Campus Gossip” የተሰኙ አምዶች እንደነበሩት፣ የተማሪ አድራሻ መዝገብ (Student directory) መኖርንና ሌሎች ተመሳሳይ ርእሶችን የያዙ ዛሬ የሚያስገርሙን ነገሮችን የዘገቡ ብዙ ጽሁፎች መኖራቸውን ማሳሰብ ያስፈልጋል፡፡

በመጀመሪያ በእንግሊዝኛ ብቻ “Struggle” ÷ በኋላ ደግሞ በአማርኛና በእንግሊዝኛ "ታገል/Struggle" ተብሎ ይታተም የነበረው የተማሪ መጽሔት በአብዛኛው የፖለቲካ ቅስቀሳና የርእዮተ ዓለም መጽሔት ነበር፡፡ <u>Something</u> እና <u>እንዲህ ነው</u> ደግሞ የስነጽሁፍ መጽሔት መሆናቸውን አውጀው የወጡ መጽሔቶች ናቸው፡፡ University College Journalም የስነጽሁፍ መጽሔት ነኝ ብሎ እስሙ አኳያ ባይጽፍም ብዙ የስነጽሁፍ ሥራዎች አውጥቷል፡፡ እነዚህን÷ ጽፎ በማሳተም በኩል የነበረውን የስነጽሁፍ እንቅስቃሴ ለማጥናት መመልከት ይቻላል፡፡ ሶስቱም ዛሬ አይታተሙም፡፡ እነርሱን መሰል ሌላ መጽሔትም እስከዛሬ በዩኒቨርሲቲው አልተቋቋመም፡፡

በመጨረሻ÷ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በስምም ሆነ በቁጥር የተጠቀሱትን ጋዜጦችና መጽሔቶች ተመልክቼ ስጨርስ የተሰማኝን ከአንባብያን ጋር ለመጋራት እወዳለሁ፡፡

አንደኛ÷ በጋዜጦቹና በመጽሔቶቹ ውስጥ ይገለጹ የነበሩት የተለያዩ ሃሳቦች (የኮንሰርቫቲብ÷ የጥገና÷ የዲሞክራሲ÷ የሊብራል እና "የመሬት ላራሹ" ብዬ ልመድባቸው ለጊዜው) ብዛት አስገርሞኛል፡፡ ለብዙ ጊዜ ተማሪው በፍለጋ ላይ እንደነበርና ፍለጋው ሳያበቃ፣ የሀገሩን እውነታ

አጥንቶ ሳይዘጋጅ 1966 ድንገት እንደመጣበት ዛሬ በበለጠ ሁኔታ የገባኝ ይመስለኛል[67]። ሁለተኛ፥ ስማቸውንና መልካቸውን የማውቃቸውን ሰዎች ጽሁፎች በጨረፍታ ቃኝቼ ግማሾቹ ሕይወታቸውን መሰዋታቸውን፤ ሌሎቹ በእስር ቤት፥ በስደት፥ ሀገር ውስጥ በብስጭት፥ እና በልዩ ልዩ ሀላፊነት ላይ እንዳሉ አሰብኩ። በልዩ ልዩ መንገድ ስለተከፈለው መስዋእትነትና ከውስጡ ስለተገኘው ፍሬም አንዳንድ ሃሳቦች በአእምሮዬ ውስጥ ሽው አሉ። አንዳንዶቹ፥ ያኔ ከጻፉት በተቃራኒው አጽናፍ ላይ ደርሰው ሳይ፥ የስነጽሁፍ ተማሪ መሆኔ፥ ሌላው ቢቀር፥ የሕይወትን ጉዳይ ይበልጥ እንዳጤንበት ሰሞኑን ፍንጮች ሰጥቶኛል። ለካስ ሕይወት ይኼው ነው!!! ሶስተኛው ትዝብቴ፤ ያኔ ምንም ያላሉትን ይመለከታል። የነፍሳቸውን ባላውቅም፥ የብዙዎቹ ሥጋ በሰላም የሚኖር ይመስላል። ከዚህ የሚመነጨው ትምህርት ደግሞ ለአንድ ሀገር የሚበጅ አይመስለኝም። በሁሉም ነገር ትኙ (passive) መሆንን የሚያበረታታ የጎሊና መርዝ ይመስለኛል።

ያለአንዳች የነፍስ ውጣ ውረድ እና ስብራት፥ ተጀምሮ እስኪያልቅ ያስደሰተኝ ነጥብ ቢኖር፥ በሕይወት ዛሬ ካሉት መሀልና አሁን ብዙ ሳልጨነቅ በስም ከማስታውሳቸው፥ አስፋው ዳምጤ፥ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር፥ ሰሎሞን ዴሬሳ፥ እና ተስፋዬ ገሠሠ ተማሪ ሆነው ከስነጽሁፍ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት፥ እንደየጠባያቸውና ክሂላቸው ይዘው ዛሬም በአደባባይ በሰፊው መገኘታቸው ነው። በእውነት እነዚህን ጋዜጦች ጊዜ ወስዶ ማጥናት፥ መግቢያዬ ላይ እንደጠቀስኩት፥ በጣም ያስፈልጋል።

[67] ከዩኒቨርሲቲ ውጭ፥ በተለይ በ1960ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ ይታተሙ በነበሩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ውስጥም ይህንን አስተያየት የሚደግፉ ጽሁፎች ይታዩ እንደነበር መጠቆም ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም።